*ሐዋርያ*
*መስከረም 2000 ዓ.ም*

## <u>ርዕሰ አንቀጽ</u>

# እንደምን ነን?!
# ከዘመን ለውጥ ላይ ነን፤

በአንጡራ የዘመን ቀመራችን መሠረት፥ በዚህ የመስከረም ወር መጀመሪያ ላይ ሁለት ሺህ ዓመታት ጨልጠን ወደ አዲስ ባህረ ዘመን እንሸጋገራለን፡፡ ባለፉት ሁለት ሺህ ዓመታት ውስጥ በሀገራችን ኢትዮጵያ፥ ብሎም በዓለም አቀፍ ደረጃ አያሌ ክስተቶች በእድገትም ሆነ በጥፋት ደረጃ ተከስተዋል፡፡ ሳያቋርጡ ዓይነታቸውንና መጠናቸውን እየጨመሩ ከመጡ ዋና ዋና ክስተቶች መካከል፥ የሰው ልጅ በእደ ጥበብ እየጎለበተ በመምጣቱ ተፈጥሮንና ህብረተሰብን መርምሮ የመረዳት አቅም ማግኘቱ፥ በበጎነት ከሚጠቀሱት አውንታዊ እርመጃዎች መካከል አንዱ ሲሆን፥ በእንጻሩ ደግሞ ፍጥረተ-ሰው ሳያቋርጥ እርስ በርሱ የመጎዳዳት፥ የመተላለቅና የመጠፋፋቱ  ፍዳ ደግሞ ያለፉት ሁለት ሺህ ዘመናት ጎደሎው ህጸጽ ነው፡፡ በእደ ጥበብ እድገትና በሳይንሳዊ ምርምር የተመተረው ረጅም እርምጃ፥ ካለፉት ዘመናት በጎ ግጽታዎች ጉልህ ቦታ የያዘ ሲሆን፥ በሰው ልጆች መካከል አንዱ ለሌላው ውድመት፥ ለክብሩና ለመብቱ መረገጥ፥ ለረሃቡና ለሰቆቃው መንስኤ እየሆነ መቀጠሉ ደግሞ፥ የሰውን ልጅ ድብቅ ተፈጥሯዊ ባህርይውንና ራሱን በራሱ የማጥፋት እምቅ ሃይሉን አጉልቶ ያሳየበት ነው፡፡ ይብሱንም በየሀገሮች ባሉ ህብረተሰቦች ውስጥ እየበቀሉ ወገኖቻቸውን ረግጠው ሰብአዊ መብታቸውን የሚገፉ፥ ለረሃብና ለጉስቁልና የሚዳርጉ ጨካኝ አምባገነኖችን ሳይቋርጥ በየወራቱና ዓመታቱ ያፈራበትን ሁኔታ አስገንዝቦናል፡፡

በሀገራችን በኢትዮጵያ ደረጃ፥ ለረጅም ጊዜ ሰፍኖ የቆየው ንጉሣዊ ሥርዓት ሀገሪቱ ወደፊት እንዳትራመድ ጨምድዶ ይዞ በማዘገም፥ የዘመኑ ሳይንሳዊ እመርታ ጅራት አድርጓት የቆየ ሲሆን፥ የነበረው የውስጥ ትግል እንዴት ኢትዮጵያን እናሳድጋት ሳይሆን ለዙፋኑ ባለቤትነት እርስ በርስ  መጠዛጠዝ፥ የዙፋኑን ደህንነት ለማስከበር አይከፍሉ ዋጋ መክፈል ነበር፡፡ ለዚህም፥ ስለላው፥ ደባውና በሥርዓቱ ባኮረፉ ላይ ቅጣቱ ቀደሜታ ይሰጠው የነበር ለመሆኑ፥ የታሪካችን መዕዋል በግልጽ የሚያስረዳው ነው፡፡ ምንም እንኳ የኢትዮጵያ አያሌ ቅርሶችና አኩሪ የታሪክ ምዕራፎች የተዘገቡት ለረጅም ጊዜ ሰፍኖ በቆየው የነገሥታቱ ዘመን ቢሆንም፥ ኢትዮጵያን ያህል በተፈጥሮ ጸጋ የታደልች ሀገር ተረክቦ  ለማልማት የሚያስችላትን እምቅ ሃይል ኩርማኑን እንኳ መገልገልና በሥራ ላይ ማዋል አልተቻለም፡፡ ካለፉት ሁለት ሺህ ዘመናት ጀምሮ እስከዛሬ ሕዝባችን የተፈጥሮ ሃብቱንና አምርቶ እንዲጠቀም፥ ዘመናዊ የማምረት ስልትና ብቃት አላገኘም፤ በሚያስቆጭና በሚያሳዝን ሁኔታ ራሱን መመገብ አልቻለም፤ አምሮበት ለብሶ፥ አጊጦና ተደስቶ መኖርን አልታደለም፡፡ የዚህ ሁሉችግር ማእከል ደግሞ የሀገሪቱ የፖለቲካ ሥርዓት አለማግርና ትኩረቱ ን የሳተ የማያቋርጥ የመጠቃቃት ትግል መሆኑ ነው፡፡

የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻልና አቻቻይ ሥርዓት ለመገንባት፥ ለረጅም ጊዜ የማይናቁ ትግሎች ተካሂደዋል፡፡ በተለይም ደግሞ ላለፉት 40 ዓመታት የተካሄድው ሕዝባዊ ትግል በራሱ በታሪካችን ላይ ልዩ ቦታ የሚሰጠው ነው፡፡ የዚህ ሕዝባዊ ትግል ጽንሰስ አላማው ኢትዮጵያን ከሁዋላ ቀርነት አላቆ በሕዝቧ እኩልነት ላይ የተመሠረተና ሕዝቡን ባለሥልጣን የሚያደርግ  ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት ነበር፡፡ ይህ መሠረታዊ የሥርዓት ለውጥ ትግል ጅማሮ አዳማጩና ደጋፊው ብዙ ነበርና ለአያሌ ዘመናት ተንሰራፍቶ የቆየው ሁዋላቀር ሥርዓት ሊመክተውና ሊቋቋመው ከቶ አልቻለም፡፡ ሚሊዮኖች ገባር፥ ተጠማኝና

መብት አልባ በሆኑባት ሀገር ውስጥ፥ “መሬት ላራሹ!” “ደሞክራሲ ያለገደብ!” ..ወዘተ. የሚሉቱ ሕዝባዊ መፈክሮች ወደ ብዙሃኑ ኢትዮጵያውያን ቤት ሰተት እያሉ በመግባት በመልካም መስተንግዶ ጎዝጉዘው ስለተቀመጡ፥ ባላባታዊው የዘውድ ሥርዓት መሠረቱ ተናጋ፤ እንደመለኮት ይታይ የነበረው የዘውድ ሥርዓት፥ ሰው ሠራሽ፥ ለዚያውም አልጠግብ ባዮችና ግፈኞች ያዋቀሩት ፈራሽ ቤት መሆኑ ግልጽ ሆነ፤ ሁሉም እየተነሳ ያንቋሸሸውና ጉድፍ ይወረውርበት ጀመር፤ የሥርዓቱን መበስበስና ማክተም የተረዳው መለዮ ለባሽም፥ ፈጠን ብሎ የተፈጠረውን አጋጣሚ በመጠቀም የኢትዮጵያን የረጅም ጊዜ የዘውድ ፖለቲካን ቀለበት በመሥበር ሥልጣንን በጠመንጃ አፈሙዝ ቀልሞ ተመራርጦ ተሰየመባት::

ትግሉም መፈክሩን አድሶ፥ “ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት!” ብሎ ቀጠለ:: ፍቱን ለውጥ ፈላጊው ሕዝብና አዲሱ ወታደራዊ ሥርዓት ፊት ለፊት ተላተሙ፤ በሕዝብ ላይ በደረሰውም አረመኔያዊ ጭፍጨፋ የ ንጹሃን ደም እንደ ቦይ ውሃ ፈሰሰ፤ ለጊዜው በሕዝብ ላይ የተፈጸመው ጭካኔ የትግሉን ቱማታ የገታ ቢመስልም፥ ሕዝብ ግን በንቃትና በስልት አረመመ፤ ምን ይመጣልን ሳያውቅም ይህን ጨካኝ ሥርዓት የሚቃወሙትን ሁሉ ልቡን ክፍት አድርጎ አበረታታ፤ የጠላቱ ጠላት ሁሉ ወዳጅ አለመሆኑን ግን ከተጠቃ በሁዋላ ዘግይቶ ተገነዘበ፤ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹን የነፈገ ብቻ ሳይሆን፥ የሚገድለው፥ የሚያሥረውና የሚያሳድደው ብቻ ሳይሆን፥ ከሕይወቱ በላይ የሚሳሳላትንና የሚወዳትን ሀገሩን ከፋፍሎ ለጥፋት የሚዳርግ፥ የአባትና እናቱን ገድል የሚያጎድፍና ተከብራ የ ኖረቿውን ሀገር ለጠላቶቿ አሳልፎ የሚሰጥ በታሪካችን የመጀመሪያው ጸረ-ኢትዮጵያ መንግሥት ሥልጣን ላይ ወጣ::

ጉልበታም አውሎ-ነውጥ ዓለማችን ለእንብርክክ እያስኬዳት መሆኑ ግልጽ ነው፤ ከባድ የለውጥ ዳመና በዓለም ላይ አንዣቧል፤ ወይም ዝናብ፥ አሌያም ዶፍ መውረዱ አይቀሬ ነው ማለት ይቻላል:: በኢትዮጵያችን ደረጃም ትግሉ ቀጥሏል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለምንም ማጠየቂያ ዳር እስከዳር አሁን በሀገር ላይ የተጫነውን ሥርዓት ጠልቶታል- ይህም በ1997ቱ (እ.ኢ.ት አ) ብሄራዊ ምርጫ ተረጋግጧል:: ሕዝቡ የሚያደራጀውና የሚመራው፥ የኢትዮጵያን ህልውናና የሕዝቧን አንድነት ለመጠበቅ የቆረጠ መሪ በእግር በፈርስ ይፈልጋልና አዲሱ ዘመን ይህን የሚፈጥርና የሚወልድ፥ ያንዣበበው የለውጥ ደመናም ዝናብ የሚጥልና መሬትን በልግ የሚያለብስ ይሁን እያልን እንመኛለን:: □